# የውሸት ፌደራሊዝምን ለማስቀጠል የወያኔ መፈራገጥ

በ 1983 ዓ/ም ኢትዮጵያን ብትንትንዋ እንዲወጣ ከሻቢያና ኦነግ ጋር ወያኔ በደረሰው ስምምነት ታሪክን፤ የሕዝብ ጥንታዊ አሰፋፈርን፤ የርስ በርስ ድንበር ዘለል መደባለቅን፤ ብሎም ለበርካታ ዘመናት ፀንቶ የቆየውን ትስስር በሚያናጋ መልኩ የውሸት ፌደራላዊ ክልሎች እንዲ መሰረቱ ተድርግዋል። በ 26 ዓመት የዘረኝነት ሀጥያት በሚፈጸምባትም አገር በብዙ ሺህ የሚቆ ጠሩ ሰዎች መጤ፤ ትምክህተኛ፤ ነፍጠኛ፤ የክልሉን ቁዋንቁዋ አትናገርም፤ ዘርህ ሌላ ነው፤ ወዘተ. በሚሉ የጎጠኞች ምክንያቶች እየተለጠፈባቸው አሳዛኝና ምንግዜም የማይረሱ ጭፍጨፋዎች፤ መፈናቅሎች፤ የንብረት ዝፈፋዎችና መባረሮች ወንጀሎች ተፈፅመዋል።

በዛሬዋና እርቃንዋን በቀረችው የዘረኞች መቦረቂያ ሆና ባለችው ኢትዮጵያ በውሸት ላይ ተሞርኩዘው በተዋቀሩት ክልሎች መካከል በየግዜው የድንበርና የይገባኛል ጉዳዮች በተነሳ ግጭ ቶች ተስተናግደዋል፡ አሁንም ተባብሰው ቀጥለዋል። የግጭቶቹ ይዘተ አውዳሚ ብቻ ሳይሆን ለዘመናት ባንድነት የኖረውን ሕዝብ ቁርሾ ውስጥ በመድፈቅ ወደ መለያየት ጎራ እንዲያመሩ መን ገዱን ጠርጎላቸዋል።

ታድያ ባለፉት ሐምሌ፤ ነሐሴና መስከረም ባገሪቱ በተቀሰቀሱት ሕዝባዊ እምቢተኝነቶች የፌደራሊዝሙ አሻንጉሊትነት በገሀድ በመውጣቱ የጎጠኞቹ ሴራ ክፉኛ ተንገዳግዶ ወደ ገደል በሚያመራበት ያሁኑ ወቅት ወያኔ አዲስ የአሻንጉሊት ሕግ እደነግጋለው ብሎ ብቅ ብሎአል። ካሳ ተ/ብርሀንና የትግሬ ባለስልጣኖችን ብቻ ያካተተ "የመንግስታት ግንኙነት የፖሊሲ ማዕቀብ" ተብሎ የተሰየመ ረቂቅ ሕግ ወጥቶ ለውሳኔ ይቀርባል በሚል ዳንኪራ ተጀምርዋል። ኢትዮጵያ አለች ለሚሉ የዋሆች የረቂቁን አርዕስት ብቻ እንዲመለከቱና ያለውን ሀቅ እንዲገነዘቡ በዚች አጋጣሚ ማሳሰብ እፈልጋለው።

ረቂቁን ያዘጋጀው የፋሲል ናሆም ደቀ መዝሙር የሆነው የሕወሐት ካድሬ ዶክተር አሰፋ ፍስሀ ይባላል፡ ሰውየው ባሁን ግዜ በ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 'የፌደራሊዝም ጥናት' አስተማሪ በመሆን የ ጎጠኞቹን መሰሪ ፀረ ኢትዮጵያ አላማ ከአጋሮቹ ጋር በመሆን በከፍተኛ ት/ት ሽፋን የወያኔን ማኒፌስቶ ሕጋዊነት እንዳለው አድርጎ ሌት ተቀን ደፋ ቀና የሚል ዘረኛ ግለሰብ ነው። ከጎኑ ሆኖ በገንዘብና ባስፈላጊው ሁሉ ተሰልፎ ሽር ጉድ የሚለው ደግሞ ቀንደኛው ፀረ ሕዝብ የፌደራል ጉዳይ ሚኒስትሩ የትግራይ ትግሪኝ ፈላስፋ አቶ ካሳ ነው።

በዚህ ተንኮል ከወያኔ ጉያ ለመውጣት በንቅስቃሴ ላይ ያለችውን አገር ላንዴና ለመጨረሻ ለመበጣጠስ ከደርግ ዘመን እስከ አሁን በሚኒስትር ደረጃ የሁለት ሰው በላ አስተዳደሮችን ሕገ-መንግስት የፃፈው ዶክተር ፋሲል ናሆም በሚባል የሚታወቀው ኤርትራዊ ትግሬና የአይሁድ አማኒ ዋነኛው የአጥፍቶ ጠፊ ጎጠኞቹ አርኪቴክት ነው።

ልብ በሉ እንግዲህ ሁሉም የረቂቅ አዋጁ አሸቃባጮች ትግሬዎችና የወያኔ ካድሬዎች ናቸው።

ምን እነርሱ ብቻ፡ ሌላ ትግሬ ልጨምርላችሁ፡ ፀጋብርሀን ታደሰ ይባላል፡ ይህኛው ሰውዬ ደግሞ በካሳ መስሪያ ቤት 'የመንግስታት ግንኙነት' ዋና ዳይሬክተር ነው። እንግዲህ 'የመንግስታት' ሲባል ከውጪ አገሮች ጋር አይምሰላችሁ፡ ባገሪቱ ክልል የተባሉትን ለማመላከት መሆኑን ግንዛቤ ውሰዱ።

ብዙ ማለት አያስፈልግም፡ ባጭሩ የዚህ ረቂቅ አዋጅ ዓላማ ትግራይ ከአማራው በመውሰድ ያደለባትን መሬትና በቅማንት ዞን ሰበብ አባይን ወደፊት የርስዋ ለማድረግ የጀመረችውን ተግባራዊ ሴራ እንዲሁም ከአፋር ለምትዘርፈው ግዛት ሕጋዊ ለማስባልና በሕወሐት ማኒፌስቶ ላይ በቅዠት የተሳለችውን 'ታላቅዋን ትግራይ' ነገሮች ሳይበላሹ በአገሪቱ ክልሎች ወይም 'መንግስታት' ፍላጎትና ስምምነት የተመሰረተች ሕጋዊ አካል ነች ብሎ ለማቅረብ የተፀነሰ ሸል ተደርጎ መወሰድ አለበት። አካሄዱ የጉዶች ጉድ ሲሆን በተቀሩት ክልሎች በኩል ደግሞ የርስ በርስ ጦርነት ለማጫርና አገሪቱን ወደ የማያባራ የጎሳ ዕልቂት በመከተት የትግራይ ትግሪኝን ዋነኛና ሴጣናዊ ዓላማ የመጨረሻ ግብ ዕውን ለማድረግ የታለመ ስለሆነ  ይህ ሸል ልጅ ሆኖ ከመወለዱ በፊት የፀረ ወያኔ ትግልን ወደ የትጥቅ ትግል ከማሸጋገርና ሸሉን ከማጨናገፍ ውጪ ሌላ አማራጭ አለመኖሩን በማመን ሳናወላዳ መታገል ያስፈልጋል የሚል ፅናት መያዝ ያሻል።

አብነት ሁነኛው ነኝ !